

# Amhara Association in The Netherlands

**PRESS RELEASE**
**ጋዜጣዊ መግለጫ**
**APR-MAY 2026**

## ✊ የአማራ ድምፅ በአውሮፓ ሰማይ ስር፡- የታሪክ ጥሪ ለፍትህ!

“አገዛዙ ጥይት እያዘነበ ምርጫ መካሄድ የለበትም” በሚል ሃሳብ በመላው አለም  እየተደረገ ባለው ትዕይንተ ህዝብ ላይ የአማራ ማህበር በኔዘርላንድ ፥ ከጀርመን እና ከቤልጅየም አጋሮቹ ጋር በመተባበር በሜይ 11 በብራሰልስ የአውሮፓ ህብረት በር ላይ የተሳካ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ተችሏል።




**"የመድፍ ድምፅ ባለበት የሕዝብ ድምፅ አይሰማም፤ የሕዝብ ህልውና ከምርጫ ይቀድማል!"**

**“ሙሉ በሙሉ ጦርነት በሰፈነበት ቀጠና ዲሞክራሲያዊ ሂደት ሊኖር እንደማይችልና ይህ የይስሙላ ምርጫ የማይቻል (Impossible) መሆኑን በአንድ ድምፅ እንቃወማለን!**

የሚሉ እና ሌሎችንም የተለያዩ መፈክሮችን በማሰማት ሲከናውን የዋለው ሰልፍ አንድ ትልቅና ግልጽ መልዕክት አስተላልፎ ተጠናቋል። “ወገናችን በሙሉ ጦርነት ውስጥ ባለበት፣ ሰላማዊ ሰዎች በድሮንና በከባድ መሳሪያ በሚጨፈጨፉበት በዚህ ጨለማ ወቅት "ምርጫ እናካሂዳለን" ማለት የሕዝብን ቁስል መሳለቂያ ማድረግ ነው። ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የምናስተላልፈውም መልዕክት ይህ ነው።“

ይህ በቤልጅየም ከተደረገው ትዕይንተ ህዝብም በመቀጠል በአሜሪካ ፥ በካናዳ ፥ በአውስትራሊያ ፥ በዩናይትድ ኪንግደም እና በሌሎችም የአውሮፓ ከተሞች ቀጥሎ እንደሚካሄድ አስተባባሪ ኮሚቴዎቹ አሳውቀዋል።





Amhara Association in The Netherlands

PRESS RELEASE

ጋዜጣዊ መግለጫ

APR-MAY 2026




# የአማራ ማህበር በኔዘርላንድ አመራሮች ከኔዘርላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር መስሪያ ቤት ጋር ስላደረጉት ውይይት. . .




የአማራ ማህበር በኔዘርላንድ ከተመሰረተበት ግዜ አንስቶ ከተለያዩ የአለም አቀፍ ከሆኑ የተራድኦ ድርጅቶች እና የሃገራት የመንግስት ተቋማት ጋር በቅርበት እንደሚሰራ እንዲሁም አማራ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን የዘር ጭፍጨፋ የሚያስረዱ ደብዳቤዎችን ፥ ሪፖርቶችን እና በአካልም በመቅረብ እንደሚወያይ ይታወቃል።

በዚህም በማርች 20 በዴን ሃግ የኔዘርላንድ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ላይ ካዳረግነው ሰላማዊ ሰልፍ በመቀጠል ባስገባናቸው የተለያዩ ደብዳቤዎች የተነሳ፤ የሚኒስተር መስሪያ ቤቱ የእንወያይ ግብዣ ባቀረበው መሰረት በሜይ 18, 2026 ማህበሩን የወከሉ አራት አመራሮች በቦታው ተገኝተው ከታች የተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል።

1. የማህበሩን አደረጃጀት፥ አላማ እና ቀደምት ስራዎችን በመዳሰስ ለቀረቡ ተያያዥ ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል።

2. አሁናዊ የአማራ ህዝብ ላይ እየተደረገ ያለውን የዘር ጭፍጨፋ የሚገልጽ ፥ ከተረጋገጡ የመረጃ ምንጮች በተገኘ ቁጥራዊ አሃዝ ላይ የተመረኮዘ፥ የ22 ገጽ ሪፖርት በማዘጋጀት አስገብቷል፤ በሰነዱ ዙሪያም ሰፋ ያለ ገለጻ አድርጓል።

3. ሚኒስትር መስሪያ ቤቱም ጥገኝነት ጥያቄዎችን ፕርሰስ ለማድረግ ለሚያዘጋጀውና በቅርቡ ለሚለቀቀው የኢትዮጵያ ሃገራዊ ሪፖርት (Country of Origin Report) በዕለቱ የገባውን የአማኔ ን ሰነድ እንደማጣቀሻነት እንደሚጠቀም ቃል ገብቷል። በተያያዘም ይህንን የዘር ጭፍጨፋ አምልጠው ለሚመጡ የጥገኝነት ጠያቂዎች ከለላ እንዲሰጥ ጥያቄ አቅርቧል።

4. የተወሰኑ የማህበሩን አባላት የህይወት ምስክርትም አያይዘን በማስገባት የአማራ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን መሳደድ ለማሳየትም ተሞክሯል።

5. ይህንን የዘር ጭፍጨፋ ለማስቆም ይረዳል የተባሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን አቅርቧል። የኔዘርላንድ መንግስት ህዝባችንን ከጥፋት ለመታደግ በሚደረገው ርብርብ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ጠይቆ መግባባት ላይ ተደርሷል።

እነዚህን እና ሌሎችም ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን ከሚንስትሩ ተወካዮችም ጥሩ የሚባል ምላሾችን ተገኝተዋል፤ በቀጣይም ከማህበሩ ጋር በቅርበት እንደሚሰሩ ገልጸዋል። በዚህም እንደ ጅማሮ መልካም የሚባል ውይይት ተደርጎ ተጠናቋል።

ይህ ውይይት የተደረገው በአባላቶቻችን እና ደጋፊዎቻችን ተደጋጋሚ ሰላማዊ ሰልፎች እና የተጠናከረ ተሳትፎ በመሆኑ ማህበሩ ከዚህ በኋላም ይህንን እንቅስቃሴ አጠናክሮ እንዲቀጥል እና ከዚህም የተሻሉ ለውጦች ለማምጣት ይረዳን ዘንድ የሁል ግዜም ንቁ ተሳትፏችሁ አይለየን ሲል ያሳስባል።




PRESS RELEASE
ጋዜጣዊ መግለጫ
APR-MAY 2026

# በአማራ ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ስላለው የዘር ማጥፋት የተሰጠ አስቸኳይ ማሳሰቢያ

Lemkin Institute
for Genocide Prevention
and Human Security

የለምኪን የዘር ማጥፋት መከላከያ ተቋም (Lemkin Institute for Genocide Prevention) በኢትዮጵያ በአማራ ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ስልታዊ እና ሰፊ የዘር ማጥፋት ወንጀል አስመልክቶ ጥልቅ ስጋቱን በመግለጽ አስቸኳይ ማሳሰቢያ አውጥቷል። በተለይም ከ2023 መጀመሪያ አንስቶ በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ በሚመራው መንግስት፣ በመከላከያ ሰራዊት እና በሌሎች አጋር ታጣቂዎች አማካኝነት ማንነትን መሰረት ያደረገ ዘመቻ በአማራው ማህበረሰብ ላይ እየተካሄደ ይገኛል።




ዋና ዋና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና የዘር ማጥፋት ድርጊቶች፦

1. **ጅምላ ግድያ እና የአየር ድብደባ**፦ በንፁሃን ላይ የሚፈጸም የዕለት ተዕለት ጭፍጨፋ፣ ከህግ ውጭ የሆኑ ግድያዎች፣ እንዲሁም በድሮን እና በከባድ መሳሪያ የታገዙ ጥቃቶች።
2. ***ፆታዊ ጥቃት እና እገታ***፦ በሴቶች እና ህፃናት ላይ የሚደርስ ስልታዊ አስገድዶ መድፈር፣ የዘፈቀደ እስራት፣ እና ገንዘብ ለመቀበል የሚደረጉ እገታዎች።
3. **የመሰረተ ልማት ውድመት**፦ ሆስፒታሎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ እና የሃይማኖት ተቋማት ላይ ሆን ተብሎ የተከፈተ ጥቃት፤ በዚህም ከ4.4 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው ተፈናቅለዋል።
4. **አገልግሎቶችን ማቋረጥ**፦ የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦትን መከልከል፣ እንዲሁም የውሃ፣ መብራት፣ ባንክ እና የኢንተርኔት አገልግሎቶችን ማቋረጥ።

የአማራ ማህበር በአሜሪካ (AAA) እና ሌሎችም ተቋማት እንዳረጋገጡት፣ ይህ የማጥፋት ዘመቻ በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ የአማራ ተወላጆችን ኢላማ ያደረገ ነው።

የተቋሙ የውሳኔ ሃሳቦች እና ጥሪዎች፦

- የኢትዮጵያ መንግስት በአስቸኳይ ጥቃቱን አቁሞ የዘር ማጥፋት መዋቅሩን እንዲያፈርስ።
- ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጉዳዩን ወደ ዓለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት (ICC) አቅርቦ፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ እና በአጋሮቻቸው ላይ ምርመራ እንዲጀምር።
- ገለልተኛ የሰብአዊ መብት አጣሪ ቡድን ወደ ክልሎቹ ገብቶ ምርመራ እንዲያደርግ።

ተቋሙ መላው ኢትዮጵያውያን ዘር ጭፍጨፋን የሚያበረታቱ እና ከፋፋይ ትርክቶች በመተው፣ ለፍትህ እና ለህልውና በአንድነት እንዲቆሙ ጥሪውን አስተላልፏል።





# እየቀጠለ ያለው የንጹሃን ዜጎች እገታ፡ ከአዲስ አበባ ወደ ደብረ ማርቆስ ሲጓዙ የነበሩ መንገደኞች በታጠቁ ኃይሎች የመታገታቸው ጉዳይ

ከአዲስ አበባ ወደ ደብረ ማርቆስ በመጓዝ ላይ የነበረ የህዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ውስጥ የነበሩ መንገደኞች በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን፣ ገብረ ጉራቻ እና ፍቼ ከተሞች መሀል "አሊዶሮ" በተባለ አካባቢ በታጠቁ ኃይሎች ታግተዋል። አዲስ ስታንዳርድ ዘገባ መሰረት፣ ግንቦት 11 ቀን 2018 ዓ.ም (እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ሜይ 19, 2026) የ"ኤፍ ኤም" (FM) የህዝብ ትራንስፖርት አውቶቡስን በማስቆም ታጣቂዎች መንገደኞቹን ወደማይታወቅ ስፍራ ወስደዋቸዋል። ከሶስት ግለሰቦች ሁኔታ ውጪ የ34ቱ መንገደኞች የት እንዳሉ እስካሁን ያልታወቀ ሲሆን፣ የመንግስት አካላትም ስለ ድርጊቱ እስካሁን የሰጡት ይፋዊ መግለጫ የለም።



እነዚህ የታጠቁ ኃይሎች ጥቃት እና እገታ ሁልጊዜም በአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች መውጫ እና መግቢያ (አዋሳኝ) አካባቢዎች ላይ የሚፈጸም ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት ህዝቡ ከአማራ ክልል ወደ ርዕሰ መዲናዋ አዲስ አበባ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ወደ ክልሉ ለመጓዝ ከፍተኛ መከራ እያየ ይገኛል። ይህ ሁኔታ የአማራ ተወላጆችን በነጻነት የመንቀሳቀስ እና የመዘዋወር መብት ለመገደብ (ለመከልከል) የሚደረግ አንዱ መንገድ ነው። ይህ የጸጥታ ችግር ዜጎችን ለስራ እና ለሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ከመንቀሳቀስ እንዲታቀቡ ከማድረጉም ባለፈ፣ በተለይም የተሻለ እና ከፍተኛ የህክምና እርዳታ ለማግኘት ወደ ዋና ከተማዋ የሚያደርጉትን ወሳኝ ጉዞ በማስተጓጎል የበርካቶችን ህይወት አደጋ ላይ እየጣለ ይገኛል።

ይህ የቅርብ ጊዜ እገታ በአዲስ አበባ-ደብረ ማርቆስ መስመር ላይ እየጨመረ የመጣውን የጸጥታ ስጋት እና የዜጎችን እንግልት በከፍተኛ ደረጃ የሚያባብስ ነው። ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ መስመር ላይ ከአራት ወራት በፊት ሌላ የ"ኤፍ ኤም" አውቶቡስ በታጣቂዎች ተይዞ መንገደኞች ታግተዋል። በተጨማሪም በመጋቢት 2025 በአሊ ዶሮ አቅራቢያ ከ56 በላይ መንገደኞች፣ እንዲሁም በሐምሌ 2024 ከ100 በላይ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከገረበ ጉራቻ ከተማ አቅራቢያ ታግተው ቤተሰቦቻቸው ከፍተኛ የገንዘብ ክፍያ እንዲከፍሉ መገደዳቸው ይታወሳል።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በበኩሉ፣ ገንዘብን መሰረት ያደረጉ የእገታ ወንጀሎች በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመሩ መምጣታቸውን በማስጠንቀቅ አሳሳቢነቱን የገለጸ ሲሆን፣ ይህ የህዝብ የትራንስፖርት እና የዜጎች ነጻ እንቅስቃሴ ላይ የተጋረጠው አደጋ በአፋጣኝ መፍትሄ ሊሰጠው እንደሚገባ ያሳያል።






# የተረሱት 9 ሚሊዮን ተማሪዎች. . . በጦርነት እና ቀውስ ከትምህርት ገበታ የተፈናቀሉ የኢትዮጵያ ህጻናት

በአሁኑ ወቅት ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የኢትዮጵያ ህጻናት ከትምህርት ገበታቸው ርቀው ይገኛሉ። እነዚህ ህጻናት በጦርነት፥ በታጠቁ ኃይሎች ግጭት፣ በብሔር ውጥረቶች እና በከባድ የኢኮኖሚ ችግሮች ማዕከል ውስጥ ተዘፍቀው ይገኛሉ።

**የችግሩ ስፋት እና አሳሳቢነት**

በ2023 መረጃ መሰረት፣ ከጠቅላላው የሀገሪቱ ትምህርት የደረሱ ህጻናት መሀል ከ35% በላይ የሚሆኑት ወደ ትምህርት ቤት አልገቡም። በህዳር 2024 በወጣው መረጃ ደግሞ፣ በግጭት እና በጦርነት ምክንያት ወደ 10,000 የሚጠጉ ትምህርት ቤቶች ሲወድሙ፣ ከ6,000 በላይ የሚሆኑት ተዘግተዋል።



ከእነዚህ ከትምህርት ገበታቸው ከተፈናቀሉት 9 ሚሊዮን ተማሪዎች መካከል ከ 5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት የአማራ ተወላጆች ናቸው። ይህ ሁኔታ ድንገተኛ አደጋ ሳይሆን፣ ሆን ተብሎ የአማራን ትውልድ ከትምህርት በማራቅ እና መሃይም በማድረግ በአማራ ህዝብ ላይ የዘር ማጥፋት (Genocide) ወንጀል ለመፈጸም የሚደረግ አንዱ ዋነኛ ስልታዊ መንገድ ነው።

**ከትምህርት ገበታ መቅረት የሚያስከትለው መዘዝ**

ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታ ውጭ ማድረግ የሚያስከትለው ጉዳት እጅግ የከፋ ነው፡

- **ማህበራዊ ቀውስ**፡ ህጻናትን ለጉልበት ብዝበዛ፣ ያለዕድሜ ጋብቻ እና ሌሎች አስከፊ የብዝበዛ ዓይነቶች ያጋልጣል።
- **ሀገራዊ ተጽዕኖ**፡ በሀገር ደረጃ ድህነትን ያባብሳል፣ ኢኮኖሚያዊ ምርታማነትን ይቀንሳል፣ እንዲሁም ተስፋ የቆረጡ ወጣቶችን ይፈጥርና ወደ አስከፊው የየብስ እና የባህር ስደት እንዲያመሩ ያደርጋል። በተጨማሪም ያልተማረ ማህበረሰብ ወደ ተጨማሪ ግጭቶች በቀላሉ እንዲሳብ መንገድ ይከፍታል።

**ምን መደረግ አለበት?**

መንግስት አሳሳቢውን ቀውስ ሸፋፍኖ በማለፍ ኃላፊነትን ከማሸሽ ይልቅ፣ ይህንን የትውልድ ማጥፋት ቀውስ በግልጽ አምኖ ሊጋፈጠው ይገባል። የውስጥ ግጭቶችን በሰላማዊ ዲፕሎማሲ እና በድርድር ለመፍታት ቅድሚያ መስጠት አለበት። የዓለም አቀፍ ማህበረሰብም ይህንን አደጋ በመረዳት በአፋጣኝ ለአደጋ ጊዜ ትምህርት የሚውል የሰብአዊ ድጋፍ በማድረግ ጣልቃ ሊገባ ይገባል።